# መጨረሻው ወንበር ላይ "ሰይጣን ተቀምጧል!"



(አሌክስ አብርሃም)

*አብርሃ ደስታ*

*ማሳሰቢያ ፡ - ይህ ፅሁፍ የማንንም ፖለቲካ ድርጅት ለመደገፍ ማንንም ለመቃወም አልተፃፈም ያየሁትን እንዳለ ነው ያስቀመጥኩት መልካም ንባብ!*

ቆየት ብሏል ....መቐለ ዩኒቨርስቲ ለአንድ ወርክ ሾፕ ጠርቶን ወደዛው ጎራ ብየ ነበር ....ከተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች የተሰባሰብን በእድሜም በትምህርትም ወጣት የነበርን፣ ጎልማሶች እንዲሁም በእድሜም በትምህርትም የገፉ ሙህራን አዳራሹ ውስጥ ነበሩ! ፈረንጆችም ነበሩ! አንዳንድ ወረቀቶች በተሰበሰብንበት ጉዳይ ላይ በተለያዩ ምሁራን ቀረቡና በጉዳዩ ላይ ክፍት ውይይት እንዲደረግበት ለተሳታፊው እድል ስለተሰጠ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ተሳታፊዎች የቀረቡትን ወረቀቶች በማድነቅ አስተያየት ተሰጠ። የወረቀት አቅራቢዎቹም እውቀት ትጋት እና ጉብዝና ተደነቀ! አዳራሹ በአንድ አይነት የመደናነቅና የመሞጋገስ ድባብ ተሞልቶ እያለ ድንገት ከኋላ አካባቢ የአንድ ተሳታፊ እጅ ወጣ! የመድረክ መሪው ፊት ባንዴ ጨፍግጎ እድሉን ከኋላ አካባቢ እጁን ላወጣው ሰው ሰጠ .... ብዙሃኑ ታዳሚ ወደኋላው እየዞረ ተመለከተ። አጠገቤ የነበረ አንድ የመቐለ ዩኒቨርስቲ መምህር "ይሄ ሰይጣን ሊበጠብጠው ነው" አለ! ‹ሰይጣኑ› መናገር ጀመረ! ከጎኔ የነበረው ሰው እንደፈራው ተናጋሪው አዳራሹ ውስጥ የነበረውን የመደናነቅና የመሞከሻሸት ድባብ አፈር ድቤ አስበላው!

የቀረበውን ወረቀት ሃሳብ አንድ በአንድ እያነሳ ተቸ፤ ይሻላል የሚለውን ሃሳብም አቀረበ! በከንቱ ደግፈው ሃሳቡን ሲያሞካሹ የነበሩ ምሁራንንም በሃፍረት እስኪሸማቀቁ ልክ ልካቸውን ነገራቸው! በየንግግሩ መሃል በድፍረቱና ሃሳቦቹን በሚገልፅበት መንገድ አዳራሹ በታፈነ ሳቅ ይሞላ ነበር! ከዚህ ሰው ንግግር በኋላ እንደአዲስ የጦፈ ክርክር ተነሳ! ከጎኔ የተቀመጠውን መምህር ‹‹ይሄ ሰው ማነው?›› ስል ጠየኩት። በብስጭት ፊቱ ጨፍግጎ ስሙን እየተፀየፈ ጠራው "አብርሃ ደስታ ይባላል በቃ ዋና ስራው ማራበሽ ሰላም ማደፍረስ ነው" ሲል አጭር ማብራሪያ ሰጠኝ ፊቱ ላይ ጥላቻና ብስጭት ይንቀለቀል ነበር!

ለሻይ እረፍት እንደወጣን አብርሃ ብቻውን ቁሞ ከሩቁ አየሁት .... በኋላ አንድ መቀሌ ዩኒቨርስቲ የተመደበ ጓደኛየ ሲነግረኝ አብርሃ ደስታ በአካባቢው መሃበረሰብ በተለይ ‹‹በተማረው›› ክፍል የተገፋ ሰው ነበር! ጓደኞቹ እሱ ጋር መታየት የሚያመጣባቸውን ጣጣ በመፍራት ሸሽተውታል። በጣም የተወሰኑ ሰዎች ብቻ ናቸው የሚቀርቡት፤ እንዲህ ወገቡን አስሮ ስለነፃነታቸው የሚከራከርላቸው የአካባቢው ነዋሪዎች ሳይቀሩ እንደከሃዲ ነው የሚመለከቱት! እንደውም በመንገድ ላይ ሲያልፍ ምራቃቸውን ሁሉ የሚተፉበት ግልፍተኛ የህወሃት አድናቂዎች ነበሩ!

ምክንያቱም በአካባቢው ህወሃት ሰዎች ተሰብስበው እንደመሰረቱት የፖለቲካ ድርጅት ሳይሆን መላእክት ተሰባስበው እንዳቋቋሙት የፃድቃን ማህበር ነው የሚታየው! የህወሃት ስብከት ፖሊሲና ህግ ለአካባቢው ህዝብ (ለብዙሃኑ) እንደ ሃይማኖት ቀኖና ነው፤ አይሻርም አይቃወሙትም፤ የማይከሰስ ንጉስ የማይታረስ ሰማይ ነው! በእርግጥ በጣም አልፎ አልፎ ስህተቱን የሚቃወሙ ይኖራሉ፤ ግን ያን ያህል ቦታ የሚሰጣቸው አይደሉም! ከዛም በኋላ የታዘብኩት ነገር ህወሃት በጀግንነት ተዋግቶ ፍርሃትን ህዝብ ላይ የዘራ የፖለቲካ ድርጅት መሆኑን ነው። ያኔ የተማሩና ትልቅ ደረጃ የደረሱ አንዳንድ የህወሃት ደጋፊና አባላት ሳይቀሩ አብረሃ ደስታ ሲናገር ሲስቁ እንዳይታዩ አቀርቅረው ሳቃቸውን ሲያፍኑ ታዝቢያለሁ! የሚስቁበት እንኳን ነፃነት የሌላቸው እነዛ ሙህራን በተለያዩ ጊዜያት እዚሁ ፌስ ቡክ ላይ ስለነፃነት ሲሰብኩ እየተመለከትኩ ‹በነፃነት› እስቃለሁ!

..... ከልጅነት እስከእውቀት የህወሃት ታጋዮችን ጀግንነት ታላቅነት ቆራጥነት ሃቀኝነት በተለያየ መንገድ እየተነገረው ያደገ ወጣት ... የሌሎች አገዛዞች ጭራቅነት እየተሰበከለት ከሶስት አስርተ አመታት በላይ የኖረ ህዝብ ህወሃትን መቃወምን እንደመናፍቅነት ነው

የሚቆጥረው! አብርሃም ደስታ ደግሞ ቀኖናውን ጥሶ ህወሃትን በመቃወም ‹‹ሃዊያት›› ሰርቷል!! ያውም ህወሃት ተወልዶ የጎረመሰበት ብሎም ለአቅመ መንግስት እስኪደርስ የተደላደለበት ግንባር ላይ ህወሃትን ‹‹ተሳስተሃል›› የሚል ‹‹መናፍቅ ›› ነው!

ያን ቀን እዛ አዳራሽ ውስጥ የሆነውን ነገር ከተመለከትኩ እና ብዙዎች እንዴት በጥላቻ ይመለከቱት እንደነበር ከታዘብኩ በኋላ አብርሃ ደስታ የማንንም ጥላቻና ኩርፊያ ሳይፈራ ዘና ብሎ ሃሳባቸውን ውድቅ ሲያደርግበት የነበረበት መንገድ ትዝ ሲለኝ ሰብሳቢዎቻችን በብስጭት ሲወራጩና ንግግሩን ሊያስቆሙት አስር ጊዜ ማይክ ሲወግሩ የነበረበትን ጊዜ ሳስታውስ የፖለቲካ አቋሙ ምንም ይሁን ምን ሃሰቡ ልክም ይሁን ስህተት አብረሃ ደስታ የማይናወጥ አቋም ያለው ሰው እንደሆነ አስባለሁ! እናም ባለፈው በድንጋይ ተወገረ ሲባል እስካሁን አለመወገሩ ነበር የገረመኝ!

እኔ የኢትዮጲያ ፖለቲካ ተስፋ አለው ብየ የማምን ሰው አይደለሁም! ቢሆንም ግን አብርሃ ደስታ በተስፋ ቢሱ የኢትዮጲያ ፖለቲካ ውስጥ ተስፋ ያለው ሰው ይመስለኛል! ካልታሰረ አልያም በሂወት ከቆየ! በግሌ የአብርሃን የፖለቲካ አመለካከት ሳይሆን ፅናቱን አደንቃለሁ!! በዛች ቅፅበት ‹‹ጣድቃን ነን›› የሚሉ ምሁራንና የድርጅት አባላት ‹‹መጨረሻ ወንበር በተቀመጠው ሰይጣን ›› ሲደነባበሩ ማየቴ ትዝ የሚለኝ ዛሬም አብርሃ ደስታ ፌስ ቡክ ላይ አንድ ቃል ሲናገር የሚንጫጩትን ውል አልባ ጩኸት እና ስድብ የሚያዘንቡትን ሰዎች ስመለከት ነው !

ለማንኛውም የአብርሃም ደስታ አይነት ፅናት ለአንድ የፖለቲካ ሰው ወሳኝ መሳሪያ ነው የሚያራምደው የፖለቲካ አቋም ሌላ ነገር ሁኖ!